**<u>መመሪያ ቁጥር 933/2015</u>**

## <u>የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከል ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 933/2015</u>

የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከልና የሚያስከትለው ጉዳት ለመቀነስ ስለሚወሰዱ ክልከላዎች እና ግዴታዎች በተመለከተ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረዉን መመሪያ ቁጥር 882/14ን አሁን ካለው የወረርሽኙ ነባራዊ ሁኔታ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመድኃኒትና ምግብ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 አንቀፅ 72 ንዑስ-አንቀፅ (2)፣ በምግብ፣ መድኃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 661 አንቀፅ 55 ንዑስ-አንቀፅ (3) እና የምግብ፣ የመደኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006 አንቀፅ 98 መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

### 1. <u>አጭር ርእስ</u>

ይህ መመሪያ "**የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከል የወጣ መመሪያ ቁጥር 933/2015** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

### 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ኮቪድ-19" ማለት በዓለም የጤና ድርጅት በይፋ በዚህ ስም የሚጠራው ተላላፊ በሽታ ነው።
2. "ስብሰባ" ማለት ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም፣ ለመነጋገር፣ ስልጠና ለመስጠት፣ ለመወያየት፣ ግንዛቤ ለማስጨበጥ፣ ወይም መሰል ተግባራትን ለማከናወን የአንድ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ውጪ አራትና ከዚያ በላይ ሆኖ ከሁለት ሰዓት በላይ በቤት ዉስጥ ወይም ድንኳን በመሳሰሉ በተከለለ ሁኔታ በአካል መገኘት ማለት ሲሆን እንደ አግባብነቱ እንደ ሠርግ፣ ምርቃት፣ እና መሰል የማህበራዊ ዝግጅቶች ለማድረግ የሚደረግ መሰባሰብም ያጠቃልላል።
3. "የኮቪድ-19 ምልክቶች" ማለት በኮቪድ-19 የተያዘ ሰው ላይ ሊስተዋሉ የሚችሉ እንደ ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ የሳል፣ ጣዕምና ሽታን መለየት አለመቻል፣ የጉሮሮ አካባቢ ቁስለቶች እና የመሳሰሉ ምልክቶች ናቸው።
4. "ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች" ማለት ለኮቪድ 19 እና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የበለጠ ተጋላጭ የሚሆኑ በማረሚያ ቤቶች ፤ በስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ፤ በተፈናቃይ ማቆያ ጣቢያዎች ፤ በአረጋዉያን መጦሪያ ሥፍራዎች፣ በማገገምያና የአእምሮ ህክምና ማዕከላት እና የመሳሰሉት ቦታዎች ውስጥ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው።
5. "ተቋም" ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ማንኛዉም በግል ፣ በመንግስትና መንግስታዊ ባለሆነ ድርጅት የሚተዳደር ሕጋዊ ዕዉቅና ያለው ተቋም ነው።

6. በወንድ ፆታ የተገለጹት አነጋገሮች የሴትንም ፆታ ያካትታሉ፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ አገሪቱ የኮቪድ 19 ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል::

## 4. የተከለከሉ ተግባራት እና ግዴታዎች

1. ማንኛውም ኮቪድ-19 እንዳለበት የተረጋገጠ ሰው ቫይረሱ እንዳለበት እያወቀ ወደ አገር ውስጥ መግባት፣ ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል ወይም ቫይረሱ ወደ ሌሎች ሰዎች ሊተላለፍ በሚችልበት ሁኔታ ከሌሎች ሰዎች ጋር መገናኘት የተከለከለ ነው፤

2. ማንኛውም የኮቪድ 19 ምልክቶች የታየበት ሰው የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ በአግባቡ የማድረግ ፣ ራስን በራስ በፈጣን የኮቪድ 19 ምርመራ ማድረግ ወይም በጤና ተቋም ምርመራ በማድረግ ዉጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ ለሚመለከተው አካል በፕሮቶኮሉ መሰረት ሪፖርት እና ክትትል የማድረግ እንዲሁም አጠቃላይ የኮቪድ 19 መከላከያ ተግባራትን የመፈፀም ኃላፊነት አለበት፡፡

3. ማንኛውም የኮቪድ-19 ፖዘቲቭ የሆነ ሰው እንደህመሙ ክብደት የጤና ባለሞያ በሚወስነው አግባብ ከበሽታው አስኪያገግም ድረስ በቤቱ ውስጥ ወይም በጤና ተቋም እራሱን ለይቶ የማቆየት ሃለፊነት አለበት፡፡

4. በማንኛዉም የጤና ተቋም ሠራተኛም ሆነ ተገልጋይ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜም ሆነ በተቋሙ ዉስጥ በሚሆንበት ጊዜ የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ የማድረግ ጌዴታ አለበት፡፡

5. ከሚሰጡት የአገልግሎት አይነት ከተገልጋይ ጋር ፊት ለፊት የሚገናኙ በመሆኑ ለኮቪድ 19 ስርጭት ተጋላጭ የሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንደ ጤና ተቋማት ፣ ባንኮች ፣ ሆቴሎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ፣ህግ አስክባሪ ተቋማት እና የመሳስሉትተቋማት ሠራተኞቻቸው የተሟላ የኮቪድ 19 ክትባት እንዲወስዱ የማበረታት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

6. ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎች ያሉባቸው ተቋማት ሠራተኞቻቸው የተሟላ የኮቪድ 19 ክትባት የወሰዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

7. በጤና ተቋም ውስጥ በኮቪድ-19 የሚከሰት ሞት ጤና ተቋሙ አስክሬኑን በጥንቃቄ አስተካክሎና አሽጎ ለሟች ቅርብ ቤተሰብ ማስረከብና ሟች በማዕከሉ ሲገለገልባቸው የነበሩ የግል ቁሶች በጸረ-ተህዋሲያን ውህድ በማጽዳት ለቤተሰብ የማስረከብ እና ሌሎች በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው ማንዋል የተዘረዘሩ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

## 5. ልዩ ልዩ ድንጋገዎች

1. ማንኛውም ሰው እና ተቋም ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2. ማንኛዉም ተቋም ሰራተኞቹ የኮቪድ-19 ክትባት እንዲወስዱ የማበረታታት እና ለዚህም ሁኔታዎች የማመቻቸት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን እንደዚሁም የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በተቋሙ እንዲተገበሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት ።

3. የበሽተዉን ስርጭት ለመከላከል በሚደረገው ጥረት በማንኛዉም ተቋም ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥበት እና ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜ ሰራተኛው ፣ ተገልጋዩ እንዲሁም በስብሰባ የሚሳተፍ ሰው እና አስተባበሪው የአፍ እና አፍንጫ መሸፈኛ እንዲያደረግ እና በርና መስኮት ክፍት በማድረግ በቂ የአየር ዝዉዉር እንዲኖር እንዲያደረግ ይመከራል።

## 6. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው መመሪያዎች

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጣር ስለሚወሰዱ ክልከላዎች እና ስለሚጣሉ ግዴታዎች ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 882/ 2014 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

## 7. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበትና ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**መሳይ ሃይሉ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት**

**ዋና ዳይሬክተር**